# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 187 ታህሳስ 5 2004 ገጽ 1


**የዋካው ወጣት፣ መምህር የኔሰው ገብሬ**

*በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችልም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!! እኔ ለእናንተ አርዓያ ለመሆን እሞታለሁ!!! እናንተ ታግላችሁ ነፃ ውጡ!!!*

**ብሎ በራሱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ ተቃጥሎ የሞተው። መች ነው እኛስ መሮን የምንነሳው?**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መለስ ዜናዊ የአፍሪካን የአካባቢ ጉባኤ ለመምራት የሞራል ብቃት የለውም ሲሉ አንድ ደቡብ አፍሪካዊት ጸሀፊ ገለጡ

ጃኒስ ዊንተር የተባሉት ጸሀፊ ደይሊ መቨሪክ በሚባለው የደቡብ አፍሪካ ጋዜጣ ባወጡት ጽሁፍ፣ በደርባን የተካሄደው ኮፕ 17 የአካባቢ ጥበቃ ጉባኤ፣ ድንቅ የተባለ ስምምነት አድርጓል። በጸሃፊዋ አመለካከት የስምምነቱ ዋና ድል ተብሎ የተቆጠረው ደግሞ፣ የአካባቢ ጥበቃ ለማካሄድ የተፈቀደው ገንዘብ ነው።

የአፍሪካ ህብረት አምባገነኖች ዋና ተደራዳሪያቸው አድረገው ከ2 አመት ገደማ በፊት የሰየሙት ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በጉባኤው ላይ ለአካባቢ ጥበቃ ተብሎ የተመደበው ገንዘብ አዲስ ገንዘብ አለመሆኑን ይልቁንም ከዚህ ቀደም ለእርዳታ ተብሎ ከተያዘው ላይ የሚሰጥ መሆኑን በመጥቀስ ሀብታም አገሮች ከፍተኛ ገንዘብ እንዲመድቡ ተማጽኖ አቅርቦ እንደነበር ተገልጾአል።

"ምንም እንኳ "ይላሉ ጸሀፊዋ ሲቀጥሉ" አፍሪካ በአየር ለውጥ ምክንያት ዋናዋ ተጎጂ አገር ብትሆንም፣ የተፈቀደው ገንዘብ ግን አምባገነኖችን በስልጣን ላይ ለማቆየት መዋል እንደሌለበት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

መለስ ዜናዊ በአገሩ ውስጥ የሰብአዊ መብቶችን የረገጠ፣ ጋዜጠኞችን፣ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በጸረ ሽብርተኝነት ስም ለእስር የዳረገ፣ በምርጫ 97 ወቅት 199 ሰዎችን የገደለ፣ የእርዳታ እህልን ለፖለቲካ ድጋፍ መግዢያ ያዋለ፣ በቅርቡ ይፋ በሆነው የግሎባል ፋይናንሻል ኢንተግሪቲ ሪፖርትም ባለፉት 9 አመታት ከኢትዮጵያ የተዘረፈ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ወደ ውጭ መውጣቱ የተረገጋጠ በመሆኑ የአፍሪካን የአየር ለውጥ ጉባኤ የመምራት የሞራል ብቃት የለውም ብለዋል ጸሃፊዋ።

ይህ ገንዘብ መለስ ዜናዊን በመሳሰሉ የአፍሪካ አምባገነኖች እጅ የሚወድቅ ከሆነ ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሁሉ፣ አሁንም ገንዘቡ የአምባገነኖችን የስልጣን እድሜ ለማራዘሚያነት ሊውል ይችላል።

መለስ ሁለት አህዝ የኢኮኖሚ እድገት እንዳገኘ አድርጎ በማስወራት የምእራብ አገሮችን ስሜት ለመያዝ መቻሉን የገለጹት ጸሀፊዋ፣ የመለስ ዜናዊ ሁለት አህዝ እድገት እስከዛሬ በታዋቂ ኢኮኖሚስቶች አለመረጋገጡንና ነገር ግን በአለፉት 20 አመታት ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው እድገት ከ5 በመቶ እንደማይበልጥና ይህም የዕድገት አህዝ ባለፉት ተከታታይ አመታት አፍሪካ ካስመዘገበቿው አጠቃላይ 6 በመቶ እድገት ጋር ሲተያይ አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የእርዳታ ገንዘብ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ መዋሉን የሚቆጣጠር ነጻ የሲቪክ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ገንዘብ መፍቀድ ማለት እነመለስ ዜናዊ እንዲዘርፉትና ገንዘባቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

ጸሀፊዋ ለጋሽ አገሮች ገንዘቡን በትክክል የሚቆጣጠሩበትን ስርአት ሳይዘረጉ ገንዘቡን መለቀቅ እንደሌለባቸው አስጠንቅቀዋል።

## የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ገዳይ ሃይል በአኝዋክ ወገኖቻችን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ 8ኛ አመት ታስቦ ዋለ

ህዝባችንን በመሳሪያ ሃይል አፍኖ ለመግዛት መለስ ዜናዊ በልዩ ስልጠና አዘጋጅቶ ያሰማራው ገዳይ ሃይል የዛሬ 8 አመት በአኝዋክ ወገኖቻችን ላይ የፈጸመውን የዘር እልቂት ለማስታወስ የአኝዋክ ጀስቲስ ካውንስልና ጥምረት ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ በጋራ ባወጡት መግለጫ፤ በመለስ ዜናዊ የሚታዘዘው ልዩ ወታደራዊ ሃይል እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከዲሰምበር 13 እስከ 15 ባሉት ሶስት ቀናት 424 አኝዋኮችን መግደሉን አስታውሰዋል።

ከመጀመሪያዎቹ 3 ቀናት ቡኋላ በነበሩት ተከታታይ አመታት በድምሩ 1500 አኝዋኮች መገደላቸውን ይፋ ያደረገው የድርጅቶቹ መግለጫ፤ ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአኝዋኮች ላይ የወሰደው የጭፍጨፋ እርምጃ ምክንያት የአካባቢውን መሬት፣ ውሀ፣ የተፈጥሮ ጋዝና ማእድናት ለመቆጣጠር እንደሆነ ግልጽ ነው ብሎአል።

"ዛሬ አኝዋኮችን የመግደያ ቀን ነው" በሚል መፈክር ነፍስ የማያውቁ ህጻናት፣ አሮጊቶች፣ ወጣቶችና አዋቂዎች ሳይቀሩ መጨፍጨፋቸው ተደጋግሞ መዘገቡ አይዘነጋም።

ዳውህ ማክ ጊል የተባለው ጋዜጠኛ በ2003 ባወጣው ሪፖርት፣ አሜሪካ 113 አኝዋኮች መገደላቸውን ማጣራት እንደቻለች ከመግለጡም ባሻገር (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## የአንድነት ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱንና የፓርቲውን አመራሮችንም በዲሞክራሲያዊ መንገድ መምረጡን አስታወቀ

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ለሁለት ቀናት ጠቅላላ ጉባኤውን ካደረገ በሁዋላ፣ የፓርቲውን ሊቀመንበር፣ የብሄራዊ ምክር ቤት እና የኦዲትና ኢንስፔክሽን አባላትን መርጧል።የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን በሊቀመንበርነት የመረጠው ጉባኤ፣ ለብሄራዊ ምክር ቤት ከመረጣቸው 40 ሰዎች መካከል በእስር ላይ የሚገኘውን አቶ አንዱአለም አራጌን ጨምሮ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ፣ ዶ/ር ንጋት አስፋው፣ አቶ አስራት ጣሴ፣ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣ አቶ ግርማ ሰይፉ እና አቶ ስዬ አብርሃ ይገኙበታል።

ጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባውን ሲያጠቃልል ባወጣው መግለጫ፣ ገዢው ፓርቲ ህገወጥ በሆነ መንገድ ያሰራቸውን አመራሮች አቶ አንዱአለም አራጌንና አቶ ናትናኤል መኮንንን ጨምሮ ሌሎች የፓርቲውን አባላትና የህሊና እስረኞች እንዲፈታ ጠይቋል።

ፓርቲው የመጪውን ዓመታት የትግል ጉዞ የእድሳትና የማንሰራራት ዘመን በማለትም ሰይሞታል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ በምርጫ ማስወገድ አይቻልም ሲሉ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ተናግረዋል።

ዶ/ር ነጋሶ የቪኦኤ የእንግሊዝኛ ዘጋቢ ከሆነው ፒተር ሄይንላይን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጡት፣ አሁን የተዘረጋው የፖለቲካ ስርአት ምርጫ ለማካሄድ አመቺ ባለመሆኑ ያለው ብቸኛ አማራጭ ሥልጣን ላይ ያለውን ሃይል በትግል ማውረድ ብቻ ነው።

"አምባገነኖች ለረጅም ጊዜ እንደማይኖሩ አይተናል፣ የሆነ ጊዜ ህዝቡ ተነስቶ በቃችሁ ይላል። በዚህ ዓመት ላይሆን ይችላል። በሚቀጥለውም ዓመት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የሆነ ሰአት ላይ ህዝቡ ተቆጥቶ ይነሳል። ለውጥ የሚመጣውም በዚህ መልክ ነው።" ያሉት ዶ/ር ነጋሶ ኢህአዴግ ብለው የጠሩት ህወሃት ኮሚኒስታዊ አስተሳሰቡን አለመተውን በዚህም ምክንያት ራሱን ትክክለኛ እና ብቸኛ ሀይል አድርጎ በማስቀመጥ ለረጅም ጊዜ በስልጣን ላይ ለመቆየት ህልም እንዳለው አልሸሸጉም።

የአንድነት ፓርቲ ሁለት ኮከብ መሪዎቹ ከግንቦት7 ጋር በማበር በሚል የወያኔ ፈጠራ ውንጀላ በጸረ ሽብር ስም እስር ቤት እንደሚገኙ ይታወቃል።

አንዱአለም አራጌ እና ናትናኤል መኮንን ሰላማዊ ትግሉን ወደ ፊት በመግፋት ገዢውን ፓርቲ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ከትተውት እንደነበር የአደባባይ ምስጥር ነው።

## ናይጀርያ መለስ ዜናዊ በኢትየጵያ የአልቃይዳ የወታደራዊ ስልጠና ማእከል እያቋቋመ ነው ስትል ከሰሰች ፣ ይህም የወያኔ አሸባሪነት በሚገባ አጋልጦ እርቃኑን ያስቀረ ነው ተባለለት!

ቦኮ ሀራም በመባል የሚታወቀውና በናይጄሪያ የሚንቀሳቀስ አንድ ኢስላማዊ ድርጅት በርካታ አባላት በፖሊስ ከተያዙ ቡኋላ ስለድርጅታቸው መረጃ እንዲሰጡ መጠየቃቸውን የገለጸው የናይጄሪያ መንግሥት ብዙ ጊዜ ከፈጀ እልህ አስጨራሽ ምርመራ ቡኋላ የድርጅቱ አባላት ስልጠና የሚያገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ማረጋገጣቸውን ናይጀሪያ ይፋ አድርጋለች።

በቦካ ሀራም ስም ናይጀርያ ውስጥ የምንቀሳቀሰው ይህ እስላማዊ ድርጅት ዋና አላማው በናይጀርያ የሸሪያ ህግ እነዲተገበር የሚታገል ሲሆን ከአልቃይዳ ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝም በተለያዩ ጊዜያቶችም የሽብር ጥቃቶችን በመፈፀም የህይወትና የንብረት ጥፋት ማድረሱን የናይጀሪያ መንግሥት ይፋ ሲያደርግ ቆይቶአል።

ከናይጀሪያ ፖሊስ ምንጮች ተገኘ ተብሎ ይፋ የሆነው ዜና እንዳመለከተው፤ የድርጅቱ አባላት በናይጀሪያ ፖሊሶች ቁጥጥር ሥር ሆነው በተካሄደባቸው ምርመራ ምንም መረጃ ላለመስጠት ብዙ ሲያንገራግሩ ከቆዩ ቡኋላ የሚሰጡት መረጃ ይፋ እንዳይሆን ቃል በማስገባት በሰጡት ምስክርነት አባላቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጠና እንደሚሰጣቸው በማጋለጣቸው ናይጀርያ በሁኔታው እጅግ በመቆጣት ለአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ቅሬታዋን አቅርባለች።

ቦኮ ሀራም የተሰኘው የአልቃይዳ ቅርንጫፍ የሆነው የአሸባሪ ድርጅት በቋሚነት በሶማሌያና ሱዳን የማሰልጠኛ ማእከል ያሉት ሲሆን በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ አዲስ የማሰልጠኛ ካምፕ መክፈቱን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ይህው የአሸባሪው ተቋም ከመለስ ዜናዊ ጋር በመመሳጠር የአሸባሪዎች ማሰልጠኛ ካምፕ ሊያቋቁም የቻለው፣ ከምእራባዊያኑ አለም እየተከሰሰ በመጣው ጫና እነዲሁም፣ በቦኮ ሀራም እና አልቃይዳ መካከል ያለው የአላማ ትስስር በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጭምር ከታወቀ በኃላ መሆኑ ብዙዎችን አስገርሞአል።

መለስ ዜናዊ በአሁኑ ወቅት ስልጣኔን ይቀናቀኑኛል ብሎ የሚፈራቸውን ሰላማዊ ዜጎችን በአሸባሪነት እየወነጀለ በተፈበረከ ማስረጃ ወሂኒ ውስጥ እያሰቃዬ እንደሚገኝ በምዕራባዊያን ወድጆቹ ጭምር እየታወቀ መጥቶአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## “የብሄር፣ ብሄረሰቦች ቀን” - የአገር ውስጥ ቅኝ ገዢዎች ድግስ

ሰሞኑን “የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን” የሚል የማስመሰያ ስያሜ የተሰጠው ድግስ በመቀሌ ከተማ ተጥሎ ሲበላና ሲጨፈር ተከርሟል። ይህ ዓመታዊ ድግስ እንደ ነገሥታት ግብር ተገዢዎች ተገዢነታቸውን፤ ምስለኔዎች ደግሞ ታማኝነታቸውን ለገዢዎቻቸው የሚያረጋግጡበት መድረክ ነው።

ይህ በዓል የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በትግራይ ላይ ብቻ ሳይሆን በአማራም፣ በኦሮሞም፣ በሲዳማም፣ በወላይታም፣ በአፋርም፣ በሶማሊም፣ በጉራጌም፣ በሃድያም፣ በአንዋኝዋክም፣ ... በሁሉ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ላይ ያለውን “የበላይነት” ለትግራይ ሕዝብ እና ለዓለም የሚያሳይበት ቀን ነው።

ድግሱን ለማድመቅ ከየማኅበረሰቡ የተውጣጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ጨፋሪዎች ወደ መቀሌ ተጉዘዋል። ታማኝነታቸውን የሚመሰክሩ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ምስለኔዎች ከዋነኛቹ የበዓሉ ባለቤቶች እኩል ሽር ጉድ ሲሉ ሰንብተዋል። የውጭ አገር እንግዶችም በተመልካችነት ተጋብዘዋል።

የድግሱ መርሃ ግብር የሚከተለውን ይመስላል -

በቅድሚያ ነፃነታቸውን የተገፈፉ፤ በገዛ አገራቸው ሁለተኛና ሶስተኛ ዜጋ የሆኑ የኅበረተሰብ ክፍሎች እንወክላለን የሚሉ ሰዎች በትግራዩ ገዢዎችና ምስለኔዎቻቸው መረገጣቸው የፈጠረላቸውን ደስታ በመግለጽ ንግግሮችን ያደርጋሉ። ንግግሮቻቸው በፋሺስት ጣልያን ወረራ ወቅት ለጠላት ያደሩ ባንዳዎች ያደርጉት የነበረውን አንገት ሰባሪ ንግግሮችን ያስታውሱናል።
ቀጥሎ ከየክልሉ የመጡ ምስለኔዎች የትግራይ ገዢዎች በመላው አገሪቱ ባሰፈኑት አገዛዝ ስለተገኘው ልማትና ዲሞክራሲ ይደሰኩራሉ። የድግሱ መድመቅ፤ የምግቡ መትረፍረፍ፤ የመጠጡ ሞልቶ መፍሰስ፤ ይህ ልማት ባመጣው ብልጽግና ረሃብ የሚገርፈው፣ የኑሮ ውድነት የሚለበልበው ዜጋ ታሪክ ሆኗል የሚል መልእክት ማስተላፊያ ነው። የተገዥዎቹ ዲስኩር በፋሽት ጣልያን የወረራ ክፉ ዘመን የየአውራጃዎች ገዢዎች ለግራዚያኒ ያቀርቡት የነበረው ራፖርት ዓይነት ነው።
በመጨረሻም የተገዢ ማኅበረሰብ ተወካዮች ለትግራይ ገዢ ቡድን አባላት ረዥም እድሜ እየተመኙ በጭፈራና በሆታ “በነገሥታቱ” ፊት በሰልፍ ያልፋሉ።

ይህ ነው “የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን” የሚል የማስመሰያ ስም የተሰጠው ድግስ። ኢትዮጵያዊያን ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንዲህ ዓይነቱን አዋራጅ ድግስ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት ያውቁታል። የአሁኑ ልዩነቱ ወራሪዎችና ተወራሪዎች፤ ቅኝ ገዢዎቹና ቅኝ ተገዢዎች በመልክ መመሳሰላቸው ብቻ ነው። በተግባር ረገድ ፋሽስት ጣሊያን ከሠራው ግፍ በላይ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ዛሬ እየሠራ ነው።

ይህንን ሃቅ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የተሰወረ አይደለም። ለመሆኑ

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ወርሮ የያዘውን አገር ከራሱ ብቻ በወጡ ሰዎች በሚመራ ሠራዊትና የስለላ ተቋም አማካይነት እየገዛ መሆኑን የማያውቅ ማነው?
በሃብት ዘረፋውስ ቢሆን መዝባሪው ማን፤ ተመዝባሪው ማን እንደሆነ ለይቶ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ?
እስር ቤቶች ውስጥ አሳሪውና ደብዳቢው ከየት የመጣ እንደሆነ፤ ታሳሪውና ተደብዳቢው ደግሞ ማን እንደሆነ የማያውቅ ማነው?
መሬት ቢታደል፤ ጨረታ ቢወጣ፤ ብድር ቢሰጥ፤ የትምህርት ወይም የሥራ እድል ቢኖር ቅድሚያው የማን እንደሆነ እስካሁን የማያውቅ የዋህ አለ?

ይህንን የአረጀ፣ የበሰበሰ ከቅኝ ገዥዎች ሰነድ የተገለበጠውን አሠራሩን ነው መለስ ዜናዊ “ፌደራላዊ፣ ዲሞክራሲያዊ” እያለ የሚያቆላምጠው። ይህንን የዜጎች ራስን አዋራጅ የተገዢነት ማረጋገጫ ዝክርን ነው “የእኩልነት ማረጋገጫ” የሚለው።

በዝምታ የመገዛታችንን ውጤት ግን እያየነው ነው። በየዓመቱ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በትዕቢት ይበልጥ እያበጠ፤ የተገዢዎች ውርደት ደግሞ እየባሰ ነው። የኦሮሞና አማራ ማኅበረሰቦች ለይስሙላም ቢሆን ከሥልጣን መባረራቸውቸው የዚህ ዝምታው ውጤት ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በስፋት የተያዘው ታሪክን ከልሶ የመፃፍ ፕሮጀክት ሌላው የዝምታ ውጤት ነው። በአዲሱ ታሪክ መሠረት ትግራዋይ ሁሉ ጀግና፤ ሌላው ሁሉ ፈሪ ነው። በአዲሱ ታሪክ መሠረት በቀድሞው ሥርዓትም ቢሆን የትግራይ መሳፍንትና ነገሥታት ደጋግ፣ ተጠቂዎች እና ተበዳዮች ናቸው። በአንፃሩ የአማራ መሳፍንትና ነገሥታት በሙሉ መሰሪዎችና ክፉዎች ናቸው። ይህ መንገድ የት ያደርሰናል?

በትግራይ እና በተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ቅራኔ ለማስረጽ መለስና ቡድኑ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። የተመኙትን ያህል ባይሆንም ጥረታቸው መና እንዳልቀረ ማየት ይቻላል። እነሆ መቀሌ ድረስ ተጉዘው ተገዢነታቸውን በደስታ የሚናገሩ ሰዎችን አፍርተዋል። በዚህ ደረጃ ራሳቸውን አዋርደው ብሄረሰቦቻቸውን እንዲያዋርዱ በማድረግ ለሚፈጸመው ወንጀል የሃገሪቱ ህዝብ በዋንኛነት ተጠያቂ የሚያደርገው የትግራዩን ገዥ ጉጅሌና ከዚህ ጉጅሌ ጋራ በመጠጋት ከየትኛውም የሃገራችን ማህበረሰብ ክፍል እጅግ የላቀ ከፍተኛ የስልጣንና የጥቅም ተካፋይ የሆነውና እየሰፋ የመጣውን የትግራይ ገዥ መደብ ነው። ይህ አካሄድ አገራችንን የት ያደርሳት ይሆን የሚለው ስጋት ከኢትዮጵያዊያን አልፎ የውጭ አገር ሰዎችን ጭምር እያሳሰበ ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ከሥልጣን ካላባረርን አባቶቻችና እናቶቻችን ከአምሳ ዓመታት በፊት ያባረሩትን ቅኝ ተገዢነት፤ የደቡብ አፍሪካ ዜጎች ከ15 ዓመታት በፊት የተገላገሉትን የአፓርታይድ ፌደራሊዝም ለልጆቻችንና ለመጪው ትውልድ ማውረሳችን የማይቀር ነው።

ይኸ ሁሉ በደል አስመርሮት ነው የዳዉሮ ዞን፣ የዋካው ወጣት፣ መምህር የኔሰው ገብሬ

> *በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልቻልም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልቻልም!!! እኔ ለእናንተ አርዓያ ለመሆን እሞታለሁ!!! እናንተ ታግላችሁ ነፃ ውጡ!!!*

ብሎ በራሱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ ተቃጥሎ የሞተው። መች ነው እኛስ መሮን የምንነሳው?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁላችንም እንደ መምህር የኔ ሰው ገብሬ “በደል በዛ!!!” ብለን አምርረን እንድነሳ ሆኖም ክንዶቻችንን በራሳችን ላይ ሳይሆን በበዳዮች ላይ እንዲሆን ያሳስባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

................................................................................................

## የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ገዳይ ሃይል በአኝዋክ ወገኖቻችን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ 8ኛ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አገዛዝ የዘር ማጥፋት ወነጀል ለመፈጸም ሙከራ ማድረጉን የአይን እማኞችን አነጋግሮ ዘገባ ማቅረቡ ይታወሳል።

በ2004 ሰርቫይቨርስ ራይትስ ኢንተርናሽናልና ጄኖሳይድ ወች የተባሉት አለማቀፍ ድርጅቶች የጸጥታው ምክር ቤትና የአፍሪካ ህብረት በጋምቤላ ክልል እየተፈጸመ ያለውን ጭፍጨፋ እንዲያስቆሙ ጠይቀዋል።

ሂውማን ራይትስ ወች በ2005 ባወጣው ሪፖርት የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላት 424 አኝዋኮችን መግደላቸውን፣ ከ400 በላይ ቤቶችን ማቃጠላቸውን፣ እንዲሁም በርካታ ንብረት መዝረፋቸውን ይፋ በማድረግ ጉዳዩ በሰው ልጆች ላይ በተፈጸመ ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ገልጧል።

ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በጋምቤላ የፈጸመውን ዘግናኝ እልቂት በወቅቱ ለመደበቅ የቻለውን ሁሉ ጥረት ቢያደርግም በክልሉ ተወላጆች አማካይነት ዜናው አፈትልኮ ከወጣ ቦኋላ ያስከተለውን አለም አቀፍ ትኩረት ለማድበስበስ የራሱ ታማኝ ሰዎች ያሉበትን አጣሪ ቡድን አቋቁሞ እንደነበረና ከህወሃት ቀንደኞች አንዱ በሆነው አባጻሃይዬ አማካኝነት ለወያኔ ምክር ቤት ቀርቦ የነበረው ሪፖርት ሃላፊነቱን የእልቂቱ ሰልባ በሆኑት ወገኖቻችን ላይ ለማላከክ ሞክሮ እንደነበር አይዘነጋም።

ወያኔ ከጋምቤላ የዘር ማጥፋት ወንጀል ወዲህ በጋምቤላ የሚገኘውን ሰፋፊ የእርሻ መሬት ለህንድ ባለሀብቶች እዚህ ግባ በማይባል ገንዘብ እየሸነሸነ በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ ሲታወቅ ተቀማጭነቱ በአሜሪካን አገር የሆነ የኦክላንድ ኢንስቲትዩት ከሳምንታት በፊት ይፋ ባደረገው ሪፖርቱ የአካባቢውን መሬት እየተቀራመቱ ካሉት ባለሃብቶች መካከል ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑቱ የህወሃት አባላት የሆኑ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን አጋልጦአል። ከመንግሥት ባንኮች ከወለድ ነጻ የሆነ ብድር እየተሰጣቸው የጋምቤላን መሬት በነጻ እየተቀራመቱ ያሉት ህወሃቶች ለዘመናት የኖረውን የደን ተክሎች በመመንጠር ከሰል እያከሰሉ ወደጎሬቤት ሱዳን ጭምር በመሸጥ ሃብት እያካበቱ እንደሆነ ይሄው የኦክላንድ ኢንስቲትዩት ጥናታዊ መረጃ ይፋ አድርጎአል።

---

## ናይጀርያ መለስ ዜናዊ በኢትየጵያ የአልቃይዳ የወታደራዊ ስልጠና ማእከል እያቋቋመ ነው . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በምስራቅ አፍሪካ አለመረጋጋትን ፈጥሮ ሰላም አስከባሪ መስሎ ለመታየት የሚያደርገው ሙከራ በም ዕራባዊያን ዘንድ ብዙም ትኩረት ስላላገኘ የአለመረጋጋት አድማስ ወደ ምዕራብ አፍሪካ በማስፋት በንጽፅር በአህጉሩ ደረጃ ካሉት አገሮች የተሻለ መሪ ሆኖ ለመታየት ሲል እንዲህ አይነት የሌላውን አገር ተቃዋሚ የማሰልጠንና የማደራጀት ተግባር ውስጥ እንደገባ አንዳንድ የፖለቲካ አዋቂዎች ይናገራሉ።

የናይጀሪያ ፖሊስ በሰጠው ተጨማሪ መግለጫ ፣እነኚሁ ሀይላት የሰለጠኑትን አባለቶቻቸውን መልሰው ወደናይጄርየ ለመላክ ነው ትልማቸው፣ይህም ከጥርጣሬ ነፃ ለመሆን ሰልጣኞቻቸውን መጀመርያ ወደአውሮፓ ልከው በአውሮፓ ፓስፖርት ወደናይጀርያ የሚገቡበትን ሁኔታ ነው እያመቻቹ ያሉት፣ ከዚህም ባሻገር ወደአውሮፓና ዱባይ ሲላኩ አለባበሳቸወን ከህብረተሰቡ ጋር በማመሳሰል ያለጥርጣሬ የስውር አላማቸውን ከግብ የሚያደርሱበት ሁኔታ እያመቻቹ እንዳሉ አሳውቋል።

የናይጀርያ ፖሊስ ጉዳዮች ሚንስቴር የሆኑት አየር ወለድ ካፒቴን ካሌብ አሉቦላድ፣ የናይጀሪያ የደህንነት ቢሮ አመርቂ የሚባል አቀራረብ እነዳልነበረና ይህ ክስተት ግን ቢሮው በቁሳቁስ ይበልጥ እነዲደራጅ ያነቃውና አዲስ አካሄዶችን በመቀየስ የሀገሪትዋን ደህንነት ለማስጠበቅ በርትተው እነዲሰሩ እንዳደረጋቸው ጨምረው ገልፀዋል።

---

## ጉራማይሌ

(በኑረዲን - ከመርካቶ )

አገራችን ኢትዮጵያን በረጂም ዘመን ታሪኳ ዉስጥ አያሌ ነገስታት፤ሁለት ፕሬዚዳንቶችና አንድ ጠ/ሚኒስትር መርተዋታል። የእነዚህ መሪዎች በህዝብ መወደድና እነሱ ለህዝብ ያላቸዉ ክብር እንደየመልካቸዉ ይለያያል ሆኖም ብዙዎቹ መሪዎቻችን ኃይለኝነታቸዉ እንዳለ ሆኖ ብዙ የሚወደድ ባህሪይ ነበራቸዉ። ከሞላ ጎደል ብዙዎቹ የቀድሞ መሪዎች አገራቸዉን የሚወዱና ከራሳቸዉ ጥቅምና ዝና ይልቅ የአገራቸዉን ክብርና አንድነት የሚያስቀድሙ ነበሩ። ዛሬ ያልተጣለ ዕጣ ወጥቶላቸዉ አገራችንን የሚመሩት አቶ መለስ ዜናዊ ከቀድሞ መሪዎቻችን ጋር የሚጋሩት አንድ ነገር ቢኖር "መሪ" የሚለዉ ቃል ብቻ ነዉ። በተረፈ አቶ መለስ ኢትዮጵያን አይወዱም፤ ህዝብን ይንቃሉ፤ የአገር አንድነት ያፈርሳሉ፤ዘረኛ ናቸዉ፤ ተሳዳቢ ናቸዉ፤ ዉሸታምና ቂመኛ ናቸዉ። በአጠቃላይ አቶ መለስ ብዙ ነገር ናቸዉ። የእሳቸዉን አንግዳ የሆነ ባህሪይ በአንድ ጽሁፍ ማቅረብ የሚቻል አይመስለኝም፤ ለዚህ ነዉ ዛሬ ሁሉንም ጠባያቸዉን ቀላቅዬ "ጉራማይሌ" ብዬ ብቅ ያልኩት።

ትዝ ይለኛል እናቴ በልጅነቴ "ሀሁ" ስታስቆጥረኝ ወደ ፊደሉ አላይ እያልኩ ሳስቸግራት .... "ልጄ አይንኮ ካላዩበት ግንባር ነዉ" ትለኝ ነበር። አዎ አይን ካላዩበት ግንባር ነዉ። ጆሮም ቢሆን ካልሰሙበት መልኩን አሳምሮ እንደ ትልቅ ወንፊት ከአንገት በታች ከመኮፈስ ሌላ የሚፈይደዉ ምንም ፋይዳ የለም። አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ደግሞ ጆሮ መልከ ያሳምራል የሚባለዉ ከሰዉዬዉ ፊት ጋር ተመጣጥኖ ሲቀመጥ ነዉ እንጂ እንደ ኮባ ቅጠል ሰፋ ብሎ ከተንዠረገገማ ጭራሽ የዕድሜ ልክ ቅጽል ስም ያስሰጣል እንጂ ለመልክም ቢሆን አይበጅም። ደሞ ዛሬ ምነዉ ጆሮ ጆሮ አሰኘህ ትሉኝ ይሆናል። ወገኖቼ አትፍረዱብኝ - "የቸገረዉ እርጉዝ ያገባል የባሰበት እመጫትዋን" እንደሚባለዉ እኔም ብሶብኝ ነዉ ጆሮ ደግፍ እንደያዘዉ ሰዉ ጆሮ ጆሮ የሚያሰኘኝ እንጂ ወድጄማ አይደለም። የአገር መሪ ናቸዉ ብዬ እንደ ሞዴል የማያቸዉ ጠ/ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በሬዲዮ ስሰማቸዉ ስድብ፤ በቴሌቪዥን ስመለከታቸዉ ስድብ በጋዜጣም ሳነባቸዉ ነገረ ስራቸዉ ሁሉ ስድብ ብቻ ሆነብኝና ሬዲዮኑንም፤ ጋዜጣዉንም ቴሌቭዥኑንም ተዉኩላቸዉና አላነብብ አልሰማ ነገር ኮሌጅ የጨረሰ መሀይም ሆኜ ቀረሁ። ዝንተ አለሙን አይነ ስዉር ሲመራዉ ሰጥ ለጥ ብሎ የሚመራ አይናማ ዕጣ ፈደሉ አይነ ስዉር መሆን ነዉና ኮሌጅ የጨረሰ መሀይም መሆኔ ብዙም አልገረመኝም። ይልቁን እኔን የገረመኝና እንዳረረ ማሽላ የሚያንጫጫኝ ባለፈዉ ሰሞን እኚሁ ጉደኛ ጠ/ሚኒስቴር ፓርላማ ዉስጥ ያቺን ሁሌም ወደ ሌላ ሰዉ እንጂ ወደራሳቸዉ ዞራ የማታዉቀዉን ሌባ ጣታቸዉን ወደ ፓርላማዉ አባላት ቀስረዉ ያደረጉት ንግግር ነዉ። ጠ/ሚኒስትሩ እንዲህ ነበር ያሉት - "የኢትዮጵያ መንግስት ማየትና መስማት የተሳነዉ መንግሰት አይደለም፤ ማየትና መስማት የሚችል መንግስት ነዉ" እኚህ ችኮና ከራሳቸዉ ዉጭ ማንንም የማይሰሙ ጠ/ሚኒስቴር እዉነትም የሚሰማ ጆሮና የሚያይ አይን ቢኖራቸዉ ኖሮ የሃያ ሰባት አመቱ ወጣት የኔነህ ገብሬ እሳቸዉ ሆን ብለዉ በፈጠሩት ዘረኛ ስርዐት ዉስጥ ከመኖር ሞት ይሻላል ብሎ እራሱን በእሳት አቃጥሎ መሞቱን ሰምተዉ እራሳቸዉን ይመረምሩ ነበር። ወይ ጉድ! እኔ ነኝ ነገር የማይገባኝ ዕብድ እንጂ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊማ የህዝብ ጆሮ ለመዝጋት አንጂ ህዝብን ለመስማት መች ተፈጠሩና ነዉ!

እኔ አስከማዉቃቸዉ ድረስ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጆሯቸዉ ወለል ብሎ የሚከፈተዉና አሳቸዉም እያንዳንዷን ድምፅ የሚሰሙት ይህ አላግባብ ከሃያ አመት በላይ የተቀመጡበት የስልጣን ወንበር ሲነቃነቅ ብቻ ነዉ። ክቡር ጠ/ሚኒስቴር አቅጪን ልንገርዎት - እንኳን ሌባ ጣትዎን ሰዉነትዎ ላይ ያሉትን ጣቶች ሁሉ እንደቀሰሩ ቀመዉ ይቀሯታል አንጂ ይህ መነቃነቅ የጀመረዉ ወንበር መሰበሩ አርሶና እረስዎ የፈጠሩት ዘረኛ ስርዐትም መፈራረሱ አይቀርም። በእርግጥ የኢትዮጵያ መንግስት የሚሰማ መንግስት መሆኑን መናገር ከፈለጉ የህዝብን ድምፅ ይስሙ፤ የህዘብ ድምፅ ደሞ "በቃ" ነዉ የሚለዉ። በቃ!

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . እርሶና መንግሰትዎ ማንንም እንደማትሰሙ እኔም እርሶም በሚገባ እናዉቃለን። እስኪ በሚወዱት ይዤዎታለሁ። የዛሬን ብቻ ይስሙኝ- ምነዉ ጠ/ ሚኒስትር! አንዳንዴ ዋልድባም ይዘፈናልኮ!! ለሁሉም አርሶ ባይሰሙኝም እኔ አንዳንዴም ቢሆን እሰማዎታለሁና የቅርብ ግዜ ክፋትዎን ላስታዉሶት። የአገራችንን መሬት ለባዕዳን ሲቸበችቡ አይተን ምነዉ ስንሎት የሰጡን ምክንያት ከቴክኖሎጂ ሽግግሩ የሚገኘዉ ልምድና ከመሬቱ ሽያጭ የሚገኘዉ ገቢ የደሀዉን ገብሬ ህይወት ይለዉጣል የሚል ነበር። ክቡር ጠ/ሚኒስትር . . . እዉነትም የሚሰማ ጆሮ ያሎት ከሆነ በቅርቡ ኦክላንድ የጥናት ማዕከል ጋምቤላን አስመልክቶ ይፋ ያደረገዉን መረጃ የሰሙ ይመስለኛል። ማዕከሉ ጋምቤላ ድረስ ተጉዞ ባሰባሰበዉ መረጃ መሠረት ከእርሶ የሚሰማና የሚያይ ጆሮ ካለዉ መንግሰት መሬት ተረክበዉ እርሻ ከጀመሩ የአገር ዉስጥ ባለ ሃብቶች ዉስጥ ከአንዱ በቀር ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። አደራ ጠ/ሚኒስትር ይህንን የተናገሩት መኢዴፓ፤ አንድነት፤ አነግ ወይም ግንቦት ሰባቶች ሳይሆኑ አክላንድ የጥናት ማዕከል ነዉ። "ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም" ይላል የአገሬ ሰዉ . . . . ደሞ ምን ጉድ ሊያሰሙን ይሆን የኛ ጠ/ሚኒስትር? ያ ጉደኛ ፓርላማዎ እንደለመደዉ አክላንድ የጥናት ማዕከልንም "ሽብርተኛ" ብሎ ፈረጀዉ እንዳይሉኝና እንዳያስቁኝ። ለመሆኑ በኦክላንድ የተነሳ ወዳጅዎ አሜሪካንንም የሽብርተኞች ተባባሪ ብለዉ ይሰይሟት ይሆን? ወይስ የጥናት ማዕከሉ አስመራ ዉስጥ ግብር ከሚበሉትና በአኬልዳማ ቍጥር ሁለት ድራማ ዉስጥ ከሚካተቱት "ፀረ ኢትዮጵያ" ሃይሎች ዉስጥ አንዱ ነዉ? ክቡር ጠ/ ሚኒስትር ለመሆኑ እየሰሙኝ ነዉ? የሚሰሙኝ ከሆነ እባክዎ መልስ ይስጡኝ!

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . የእርሶ ነገርኮ ሲቀምሱት የሚመር ሲሰሙት የሚገርም ነዉ። ለመሆኑ ለምለም መሬት ባዩ ቁጥር ወለል ብላ የምትታዮት ትግራይ ብቻ ናት እንዴ? የሚገርመዉ ነገረ ስራዎ ሁሉ እንደ አገር መሪ ሳይሆን "ከራቀህ ሳብ" "ቀረብ ሲል ሽብ" እንዳለዉ ሌባ ነዉ። ወልቃይት ጠገዴ ለትግራይ ቅርብ በመሆኗ ከጎንደር ሳብ አድርገዉ ትግራይ ዉስጥ ሸጎጧት። ጋምቤላ ግን ሳብም ሽብም ለማድረግ አልመች አለችዎት መሠለኝ ባለሐብቶችን ከትግራይ እየጎተቱ ያሰፍሩባት ጀመር። ምነዉ ክቡር ጠ/ ሚኒስትር? ኧረ እየተስተዋለ! ሌላ ሁሉ ቢቀር ይህ በልጅነትዎ የተጠናወቶት ዘረኝነት እንዳለ ሆኖ ምነዉ ኦሮሞዉን፤ አማራዉን፤ ጉራጌዉን፤ሱማሌዉንና ይህንን ብሔር፤ብሔረሰብና ህዝብ እያሉ የሚጠሩትን ህብረተሰብ አንዳንዴ አይንዎ ቢመለከተዉ? ወይስ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥሩ ስንት ነዉ ተብለዉ ቢጠየቁ እርሶም ያንን በቀድሞዉ ንጉሳችን ላይ የምንቀልደዉን አይነት መልስ ሊሰጡን ነዉ?

ክቡር ጠ/ሚኒስትር . . . መቼም የእርሶ ጉድ ብዛቱና የሰማይ ስፋቱ መጠን የለዉምና እስኪ እሱን ትቼ አንድ የቆየ ነገር ላስታዉሶት! ለመሆኑ አንድ አገራቸዉን የሚወዱ የትግራይ ተወላጅ ወያኔን አንዲቀላቀሉ የቀረበላቸዉን ጥያቄ አስመልክቶ ከእርሶ ጋር ያደረጉት ምልልስ ትዝ ይሎታል? ምናልባት በስራ ብዛት የተነሳ ረስተዉት ከሆነ እስኪ እኔ ላስታዉሶት! ጉዳዩ እንዲህ ነዉ። እርሶ እንግሊዝ አገር ስልክ ይደዉሉና ኢትዮጵያዊዉን ምሁር አብረን እንስራ ብለዉ ይጋብዟቸዋል። ምሁሩም - ለመሆኑ ይህ አንተ የምትመራዉ የአናሳዎች አገዛዝ በዚህ መልኩ ሃምሳ አመት የሚቆይ ይመስልሃል ብለዉ ጥያቄዎን በጥያቄ ይመልስሎታል። ክቡር ጠ/ሚኒስትር በዱሪዬ ቋንቋ ሲሳደቡ በአይኔ በብሌኑ አይቻለሁ፤ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲንቁና ሲያንቋሽሹ በጆሮዬ ሰምቻለሁ ፤አብሮ አደግ ጓደኞቼ በእርሶ ትዕዛዝ ሲገደሉ ተመልክቻለሁ። ሆኖም ለእኚያ እንግሊዝ አገር ለሚኖሩት ኢትዮጵያዊ ምሁር እንደመለሱት መልስ የእርስዎን ማንነት እዉስጥ አንጀትዎ ድረስ ዘልቆ ያሳየኝ ምንም ነገር የለም። ክቡር ጠ/ሚኒስትር . . . የኢትዮጵያ ህዝብ የእርሶን ማንነት ተረድቶ ለመብቱና ለነፃነቱ ትግል ከጀመረ የቆየ ቢሆንም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደኔ ሆዱ ቆርጦና አንደ የኔነህ ገብሬ በህይወቱ ተወራርዶ እንዲታገልዎ ስለምፈልግ ያንን የእርሶን የዘፈቀ ዘረኝነት በግልፅ የሚያሳየዉንና አንግሊዝ አገር ለሚኖሩት ምሁር የመለሱትን አሳፋሪ መልስ ከነጥያቄዉ አንዳለ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ።

ሀሎ-ኢትዮጵያ በእድገት ጎዳና በመገስገስ ላይ ናትና ለምን ወደ አገርዎ መጥተዉ ይህንን የጀመርነዉን ጉዞ ከግቡ አያደርሱም?

ስለ እድገትና መረጋጋት ከማዉራታችን በፊት አንድ ጥያቄ ልጠይቆት . . . . ለመሆኑ ይህ እርሶ የሚመሩት የአናሳዎች አገዛዝ በዚህ መልኩ ለሃምሳ አመት የሚቀጥል ይመስሎታል?

"አይመስለኝም ! ሆኖም ሃምሳ አመት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ የትግራይን ህዝብ እንደ አይሁድ ህዝብ ማድረግ እችላለሁ"

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . እንግዲህ ይታዮት እርሶ በአንድ በኩል የድፍን ኢትዮጵያ መሪ ነኝ ይላሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጥረትዎ ሁሉ ትግራይን እስራኤል ለማድረግ ነዉ። ምነዉ ጠ/ሚኒስትር? እኛ የተቀረነዉ ኢትዮጵያዉያን ከህዳሴዉ ወተት ስልባቦቱ ከፌዴራሊዝም እኩልነት ዘፈኑ ብቻ ነዉ እንዴ የሚደርሰን? ለመሆኑ የትግራይ ዉድቀት ወድቀቴ የትግራይ ልማት ልማቴ መሆኑን ያዉቃሉ? ዬኔ ችግርኮ እኩል አለመታየታችንና እኩል የልማት ዕድል አለማግኘታችን ነዉ እንጂ እገሌ መራኝ አልመራኝ አይደለም። ክቡር ጠ/ ሚኒስትር... እርሶና ፓርቲዎ ሽብር፤ሽብርተኛ፤ባግዳድና አኬልዳማ እያላችሁ ያሰኛችሁን ድራማ ስትሰሩ ትከርሚታላችሁ አንጂ እኛ ኢትዮጵያዉያን እኩልነታችን ተረጋግጦ የአገራችንን የፖለቲካ ሥልጣን እኩል እስካልተጋራን ድረስ የእርሶም ዕድል እንደ ጋዳፊ ቱቦ ለቱቦ ከመንከራተት የተለየ አለመሆኑን ከአሁኑ ላረጋግጥሎት እፈልጋለሁ። አሁንም የሚሰሙኝ ከሆነ እቅጩን ልንገሮት. . . . አንዳንዶቻችንን ማሰር፤ አንዳንዶቻችንን አገራችንን ጥለን እንድንሰደድ ማድረግ አንዳንዶቻችንን ደግሞ መግደል ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ምንም ያድርጉ ምን የነፃነትና የእኩልነት ፍላጎታችንን እንኳን መግደል መንካትም አይችሉም።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . እኔኮ ጭራሽ ግራ ገባኝ . . . ምን አድርጉ ወይም ምን ሁኑ ነዉ የሚሉን? ይህንን ጥያቄ የምጠይቆት ምናልባት አድርጉ የሚሉንን አድርገን ሁኑ የሚሉንንም ሆነን በሃያ አመት ዉስጥ አንድ ቀን እንኳን ከህዝብ አገር አብረዉ ብስቁ ብዬ ነዉ? መብታችንን ስንጠይቅ "ባግዳድ" እያሉ ሲኒማ ይሰሩብናል። የነፃነት ያለህ ስንል ደግሞ "አኬልዳማ" እያሉ ያልፈሰሰ ደም ያሳዩናል። ስንናገር "ሽብርተኛ"ዝም ስንል ደግሞ ጭራሽ "ሟርተኛ" ይሉናል። ክቡር ጠ/ሚኒስትር ኧረ ምን ይሻላል የእርሶ ነገርኮ ጨነቀኝ . . . እስኪ በማን ልበልዎ! በመድሐኒአለም እንዳልሎት "መድሐኒአለም" ከአገር አገር ከሰዉ ሰዉ ሳይለይ ሁላችንንም ነዉ ያደነዉ። በግሸን ማሪያም እንዳልሎት እርሶ ከወሎ ታቦት የትግራይ ጣዖት ይሻላል ባይ ኖት። ጠ/ሚኒስትር የሚሰሙኝ ከሆነ በዚያ በሚወዱት ታቦት በአቡነ አረጋዊ ይዤዎታለሁ . . . ለመሆኑ እኛ እንደርሶ ከዚያ ከወርቃማዉ ዘር ያልተወለድነዉ ኢትዮጵያዊያን ምን መስለን ነዉ የምንታዮት?

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . ባለፉት ሃያ አመታት እርሶና ፓርቲዎ የሰራችሁት ድራማ ብዛቱና አይነቱ. . . እንዴ! እነዚህ ሰዎች መሪዎች ናቸዉ ወይስ ተዋንያን የሚያሰኝ ነዉ። እርሶ ፓርላማ ዉስጥ ከሚቀልዱት ቀልድና ቃለመጠይቅ በተደረጉ ቁጥር ከሚሠሩት ድራማ ዉጭ እርሶና ፓርቲዎ የህገ መንግሰት ድራማ፤ የፌዴራሊዝም ድራማ፤የምርጫ ድራማ፤ የህዳሴዉ ድራማ አሁን በቅርቡ ደግሞ እየቆየ ሲሄድ ቴክኖሎጂዉ እየገባችሁ መጣ መሠለኝ "ባግዳድ" እና "አኬልዳማ" የሚባል በድምጽና በምስል የተቀነባበረ ድራማ ሰርታችኋል። ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . የሰራችኋቸዉ ድራማዎች ሁሉ ፍንትዉ አድርገዉ የሚያሳዩት የእናንተን ቅሌትና ባዶነት ቢሆንም ከሰሞኑ ለእይታ የበቃዉ "አኬልዳማ" ድራማችሁ ግን ለተፃፈ ህግ፤ ለአገር ባህልና ለራሳችሁ ሂሊና የማትገዙ ዛሬም በጫካ ዉስጥ ህግ የምትተዳደሩ ተራ ወንበዴዎች መሆናችሁን ነዉ የሚያሳየዉ።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . ለእኔ ወያኔና ትልቅ ከበሮ አንድ ናቸዉ። በተነኩ ቀጥር 'እሪ' እያሉ መጮህ ነዉ እንጂ የዉስጣቸዉ ባዶነት አይታያቸዉም። "ለሞኝ ተረት ስትናገር ትርጉሙን አብረህ ተናገር" ይላል የአገሬ ሰዉ . . . ወይ ጉድ! ደሞ ምን ይሁን ብላችሁ ከባዶም ባዶ መሆናችሁን አጉልቶ የሚያሳየዉን የሰሞኑን ድራማ "አኬልዳማ" ብላችሁ የሰየማችሁት? "ሞኝን ያስተምሩታል አንጂ አያሰለጥኑትም" ሲባል አስከዛሬ በጆሮዬ ነበር የምሰማዉ። አመሰግናለሁ ክቡር ጠ/ሚኒስትር. .. ዘንድሮ በእርሶ አየሁት። ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . ስለ አኬልዳማ ማን እንደነገሮት ባላዉቅም የነገሮት ሰዉ ትርጉሙን አብሮ አልነገሮትምና ይህ ሰዉ የአገር ጠላት ነዉ። ሽብርተኛ ይሏል እንደዚህ አይነቱን የአገር መሪ የሚያደናግር አደናጋሪ ሰዉ ነዉ። ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . አኬልዳማ የክህደቶች ሁሉ ክህደት እና ደም ተቀላቅለዉ የሚገኙበት ቃል ነዉ። እርሶ ደግሞ ሁሌም በክህደትና በደም ማፍሰስ የሚታሙ ሰዉ ኖትና አኬልዳማ ሞትና ክህደት የተቀላቀለበት ቃል መሆኑን ቢያዉቁ ኖሮ እርግጠኛ ነኝ ይህንን ማንነትዎን በግልጽ የሚናገር ድራማ "አኬልዳማ" ብለዉ አይሰይሙትም ነበር። አኬልዳማ መነሻዉ ከመቆሚያዉ እንዲሁም መቸቱ ከገጸ ባህሪያቱ የተደበላለቁበትና የፈጠራ ምናቡ ያልተባ ሰዉ ሰዉ የማይሸት ድራማ ነዉ። ሆኖም ሞኝ የሆነ ሰዉ እንኳን የሚሰራዉ ስራ እሱ ራሱ ሲያዩት ያስቃልና የሞኞች የፈጠራ ዉጤት የሆነዉ አኬልዳማም አስቂኝ የሆኑ ቦታዎች አሉት። እኔን ያሳቀኝና ዛሬም ድረስ ጥርሴን አላስከድን እያለ የሚያስቸግረኝ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጉራማይሌ . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

ግን ድራማዉ መግቢያ ላይ “ይህንን ፕሮግራም ከ13 አመት በታች ያሉ ህፃናት እንዲመለከቱት አይመከርም” ተብሎ በአንስታይ ፆታ የተነበበዉ ማስጠንቀቂያ ነዉ። እርግጠኛ ነኝ እኚህ ሴት ያሰኛቸዉን የመናገር ነፃነት ቢኖራቸዉ ኖሮ

አኬልደማን አይቶ መለስን ያመነ
ሰማይ አንጋጥጦ ጉም የዘገነ”                  በለዉ ይመክሩን ነበር

ከዚህ ቀደም አቶ መለስ እራሳቸዉ “ህግ” በሆኑበት አገር ፍትህ ሊኖር አይችልም ሲባል እየሰማሁ ግራ ይገባኝ ነበር። “አኬልዳማ” ምስጋና ይግባዉ አሁን ግራ መጋባቱ ቀርቶ እዉነቱ ጥርት ብሎ ታየኝ። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ ብዙ መጓዝ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። በቅርቡ በአቶ መለስ ዜናዊ አቀነባባሪነት የተሰራዉን አኬልዳማን መመልከቱ ይበቃል። ለይስሙላ የተጎለተዉ የእትዮጵያ ፓርላማ የፀረ ሽብሩን ህግ አፀደቀዉ ይባል እንጂ ህጉን የጻፉትም ያፀደቁትም አቶ መለስ ዜናዊ ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ በዚህ ህግ መሠረት ተጠርጥረዉ የታሰሩትን ግለሰቦች የከሰሱትም አቶ መለስ ዜናዊ እራሳቸዉ ናቸዉ። ዛሬ የእነዚህ የተከሰሱት ሰዎች ጉዳይ በፍርድ ቤት እየታየ ነዉ ቢባልም አቶ መለስ በአኬልዳማ ድራማቸዉ ግለሰቦቹ ሽብርተኞች መሆናቸዉን ለአለም ህዝብ በማብሰር በእርግጥም ኢትዮጵያ ዉስጥ ህጉ እሳቸዉ መሆናቸዉን አስመስክረዋል።

ብዙ አገሮች ሽብርተኛ ብለዉ የሚጠሯቸዉ እንደ አልቃይዳና አቡ ሰያፍን የመሳሰሉ ደርጅቶች የራሳቸዉን እምነትና ፍላጎት በህዝብና በመንግስት ላይ በኃይል ለመጫን መሳሪያ ጭምር የሚጠቀሙ አክራሪ ኃይሎች ናቸዉ። ደግሞም ብዙ አገሮች አንድን ሰዉ ሽብርተኛ ብሎ ለመፈረጅና እስር ቤት ለመክተት ብዙ ግዜ ይፈጅባቸዋል፤ ምክንያቱም እነሱ ሽብርተኛ ብለዉ የሚፈርጁት ሰላማዊ ዜጎችን ለማጥቃት ሲያሴር በማስረጃ የደረሱበትን ሰዉ ብቻ ነዉ እንጂ እንደኛዎቹ “ማን አለብኝ” አምባገነኖች ሠላማዊ ዜጎችን በጅምላ አስረዉ የሌለ ማስረጃ አይሰበስቡም። ለምሳሌ አሜሪካኖችና እንግሊዞች እስካሁን ድረስ በቁጥጥር ስር ያደረጓቸዉንና የመጨረሻ እርምጃ የወሰዱባቸዉን ግለሰቦች ስንመለከት ግለሰቦቹ እራሰቸዉ አሸባሪዎች መሆናቸዉን በግልጽ የሚናገሩ ናቸዉ። ለምሳሌ ከሊል ሼክ መሐመድ፤ ዘካሪያስ ሙሳዊና ብዙዎቹ ተከታዮቻቸዉ የተከሰሱበትን የሽብር ወንጀል አይክዱም ጭራሽ ትክክለኛ እርምጃ ነዉ ብለዉ ይሟገታሉ እንጂ - በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ሰዎች የሚኖሩት በየጫካዉና በየተራራዉ ስር ተደብቀዉ ነዉ። በኛ አገር ግን እነ አቶ መለስ ዜናዊ ሽብርተኛ ብለዉ የሚያስሩት አብረዋቸዉ ከተማ ዉስጥ የሚኖሩትንና ከብዕር ሌላ መሳሪያ የሌላቸዉን ጋዜጠኞች፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፤ የሲቪክ ማህበራት መሪዎችና ለህዝብ መብትና ነፃነት የሚሟገቱ ግለሰቦችን ነዉ።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር እርሶ ዉሸታም እንደሆኑ ድፍን አበሻ ያዉቃል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ችግሩ የእርሶ ዉሸት አይደለም። የህዝባችን ትልቁ ችግር እርሶን በፍጹም ማመን አለመቻሉ ነዉ። የሚገርመዉ እርሶም ሽንጥዎን ገትረዉ የሚታገሉት ህዝብ እንዳያምንዎ ነዉ መሠለኝ የኢትዮጵያ ህዝብ አዋቂዉና ህጻኑ እንደ ነጭና ጥቁር ለይቶ የሚያዉቀዉን የ1984 ዓም ዕልቂት ዛሬ በአዲስ መልክ በቪድዮ አቀነባብረዉ ሊነግሩን ይሞክራሉ።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር አኬልዳማ ላይ ያታየዉ የጭካኔ ስራ የተሰራዉ በእርሶና በጓደኞችዎ አይደለም እንዴ? እነዚያ ህፃናት በግፍ የታረዱትና አባትና እናቶቻቸዉ ገደል ዉስጥ የተወረወሩት በእርሶ ደጅአዝማችነት አይደለም እንዴ? ደግሞም ባይሆንስ? ያ ሁሉ አንኳን ለወገን ለባዳም የሚሰቀጥጥ ግፍ የተፈፀመዉ እርሶ ፈላጭ ቆራጭ በሆኑበት አገር ዉስጥ አይደለም እንዴ? ክቡር ሆይ እርሶ በድራማዉ ዉስጥ ያንን ግፍ ፈጽመዋል ብለዉ የሚያሟቸዉ ኃይሎች በወቅቱ ከእርሶ ጋር አልነበረም እንዴ ሥርግና ምላሽ የሚወጡት? ታዲያ ምንዉ ያኔ የደስ ደስ “ቺርስ” እየተባባላችሁ የጠጣችሁበት የፓለቲካ ዝቅጠት ዛሬ እነሱን ብቻ ሽብርተኛ ሊያሰኝ በቃ? ምነዉ ክቡር ጠ/ሚኒስትር? እንዳንናገር የእርሶ ጠመንጃ የለጎመዉኮ አፋችንን ነዉ እንጂ አይናችን ያያል ጭንቅላታችንም ያስባልኮ! አቤት የዉሸት ያለህ! ክቡር ጠ/ሚኒስትር ዉሸትዎ በቁመትዎ ልክ ነዉ አንዳልል የክቡርነትዎ ቁመት እንደኔ ዘለግ አይልምና ዉሸትዎን እንዳላሳንሰዉ ፈራሁ። እንደ ወላጅ እናቴም ነጭ ዉሸት እንዳልልዎት የእርሶ ዉሸት ከነጭም የነጣ ጉደኛ ዉሸት ነዉ። ክቡር ጠ/ሚኒስትር እዉነትም ለህፃናት የሚያስቡ ቢሆን ኖሮ ይህንን አገር የሚያጠፋ ዉሸት ነበር ታዳጊ ህፃናት እንዳይሰሙት ማድረግ የነበረቦት።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . “የህሜት መጨረሸዉ ስጋት የዉሸት መጨረሻዉ ዉጋት” ይባላል። ምነዉ . . . የመጨረሻዎ ታዮት አንዴ? አይዞት ላይቀርልዎ ነገር አይቸኩሉ። እርሶ ባይታዮትም እኛ እናሳዮታለን። ደግሞም እንደ ይሁዳ በክደትዎ ተጸጽተዉ ከሆነ ይሁዳ ያደረገዉን ሁሉ ያድርጉ . . . ደግሞስ ምን የቀሮት ነገር አለ? ይሁዳ ጌታዉን አንደካደ እርሶም የሚመሩትን አገር ክድዋል። ይሁዳ ጌታዉን እንደሸጠ እርሶም የአገርዎን መሬት ለባዕዳን ሸጠዋል። የቀሮት ነገር ቢኖር እንደ ይሁዳ መፀፀት ብቻ ነዉ። ክቡር ጠ/ሚኒስትር ይሁዳ እራሱን የሰቀለዉ ይህንን ሁሉ ክህደት መሸከም ተስኖት ነዉ፡ “አኬልዳማ” የሚባለዉ ቃልም ዛሬ በምናዉቀዉ መልኩ በታሪክ የተመዘገበዉ ይሁዳ እራሱን ከሰቀለ በኋላ ነዉ። ታዲያ ምነዉ እርሶ ዋናዉን ነገር ትተዉ ዘለለዉ አኬልዳማ ላይ ጉብ አሉ?

ክቡር . . . ከትላልቆቹ የአለማችን መሪዎች ከባራክ ኦባማ፤ ከአንገላ መርክልና ከኒኮላይ ሳርኮዚ ጋር በአንድ ጠረቤዛ ዙሪያ ቁጭ ብለዉ መክረዋል። የአፍሪቃን ህብረት በሊቀመንበርነት መርተዋል። በእርግጫም ይሁን በፍጥጫ ኢትዮጵያን ከሃያ አመት በላይ መርተዋል። ታዲያ መቼ ነዉ በጫካ ህግ ሳይሆን በህገ መንግስት የሚመሩት? መቼ ነዉ ቂም በቀል እንደወጠረዉ ጎጠኛ ሳይሆን እንደ አስተዋይ የአገር መሪ ማሰብ የሚጀምሩት? መቼ ነዉ የፍርሀትና የጥላቻ ድራማ ሳይሆን የፍቅርና የተስፋ ሕይወት የሚያሳዩን?

ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . ከላይ መግቢያዬ ላይ አንደነገርኮት ዕድሜ ለእርሶ የኢትዮጵያን ቴሌቪዥን መመለከት ከተዉኩ ሀዳር ሚካኤል ስድሰት አመት አለፈኝ። የሚገርሞት እርሶን በተለያዩ ገፀ ባህሪያት ከፋፍሎ የሚያሳየዉን የአኬልዳማ ድራማ የተመለከትኩት ኢቲቪ ላይ ሳይሆን “ድሬ ቲዩብ” ላይ ነዉ። አኬልዳማ ድሮም የማዉቀዉን የእርሶን ዉሸት፤ፍርሃትና ጭካኔ አረጋገጠልኝ እንጂ አዲስ ነገር አላሳየኝም። ክቡር ጠ/ሚኒስትር. . . በመጨረሻ ላም እንደሚወድዱ ስለማዉቅ እስኪ ስለ ላም ነግሬዎት ላብቃ...... ነጭ ላም ገዝተዉ ላሜ ጥቁር ናት ብለዉ ቢናገሩ ለራስዎ ይቀልሉ ይሆናል እንጂ የገዙትን ላም ያላየ ሁሉ ሊያምኖት ይችላል፤ ሆኖም የላሚቱ ወተት ጥቁር ነዉ ብለዉ ቢናገሩ ግን እንደዚህ አይነቱን ቅጥፈት ለማረጋገጥ ወተቱን መመልከት ያለብን አይመስለንም። ልብ ይበሉ እንግዲህ የእርስዎ ቅጥ ያጣ እብሪትና ቂልነት ጎልቶ የሚታየዉ እዚህ ላይ ነዉ ምክንያቱም ህዝብ የእርሶን ዉሸት ሰምቶ ዝም ባለ ቁጥር የተቀበለዉ ይመስሎታል። በቅርቡ ለእይታ የበቃዉ አኬልዳማ ድራማም የዚሁ እብሪትና ቂልነት ዉጤት ነዉ።

## በኢትዮጵያ ከሚገኘው የቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሆነ ሴራ እየተጠነሰሰ መሆኑ ተዘገበ

እግዚአብሄር ለሙሴ ጽፎ የሰጠው የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚገኝበት ቦታ ለሺ አመታት አለምን ሲያነጋግርና የበርካታ የታሪክ ተመራማሪዎችን ቀልብ ስቦ ቆይቷል፤ ያለው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ኢሳት ታዋቂው ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ግርሀም ሀንኮክ ከ8 አመታት በፊት " ዘ ሳይን ኤንድ ዘ ሲል" በሚለው መጽሀፋቸው የቃል ኪዳኑ ታቦት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኝ የሚጠቁም መጽሀፍ አሳትመዋል ካለ በኋላ በመጽሀፋቸውም የካቶሊክ እና የአይሁድ እምነት ተከታዮች አውሮፓውያን ታቦቱን ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ መመላለሳቸውን መጠቆማቸውን አውስቱአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታሪክ ባለሙያዎች፣ ፖለቲከኞችና የሀይማኖት መሪዎች፣ ለቃል ኪዳኑ ታቦት ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ ዘረኛው አገዛዝና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታቦቱን ለአለም ህዝብ ይፋ በማድረግ እውነተኛነቱን እንዲያረጋግጡ ግፊት ሲያድረጉ ቆይተዋል፡፡ የአለም ህዝብ ትኩረት በታቦቱ ላይ በአረፈበት በአሁኑ ጊዜ፣ የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ይህን እድል በመጠቀም ታቦቱን ለጉብኝት በማቅረብ ወይም በድብቅ በመሸጥ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ለማግኘት አንድ አደገኛ እቅድ እያቀደ ለመሆኑ ፍንጮች መታየት ጀምረዋል።

ቀደም ብሎ በአንትሮፖሎሎጂስቶች ዘንድ ድንቅ የታሪክ ግኝት ተደርጋ የምትቆጠረውና ኢትዮጵያ የሰው ልጆች መገኛ ናት የሚለውን ማእረግ እንድትጎናጸፍ ያስቻለቸው ሉሲ ወይም ድንቅነሽ ፣በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ ወደ አሜሪካ እንድትወጣ መደረጉ የሚታወቅ ሲሆን ድንቅነሽ ከአገር ስትወጣ በርካታ ኢትዮጵያውያንና የታሪክ ባለሙያዎች ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ማሰማታቸው ይታወሳል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በርካቶች መለስ እንደተመነው ከሉሲ ጉዞ በቂ ገንዘብ ሊያገኝ እንዳልቻለ ይገልጻሉ። ሉሲን ወደ አሜሪካ ለመላክ የተወሰደው እርምጃ ትልቅ ስህተት እንደነበር የሚናገሩት እነኚሁ አስተያየት ሰጪዎች የተገኘው ገንዘብ አነስተኛ መሆን ብቻ ሳይሆን ፣ ከእንግዲህ ሉሲ ወደ ኢትዮጵያ አትመለስም የሚለው ስጋት እንደሚያሳስባቸው ይጠቁማሉ።

የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመሳሳይ መልኩ ለኢግዚቢሽን ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ እየተወጠነ ያለው ሴራ ኢትዮጵያ በምንም ገንዘብ ሊተመን የማይችለውን ውድ ሀብቷን እንድታጣ ያደርጋታል ያለው ኢሳት የወያኔው ቀኝ እጅ አቡነ ጳውሎስ "ታቦቱን ለአለም አሳያለሁ" የሚል መግለጫ ከሰጠ በሁዋላ፣ ወዲያውኑ ከምመናን ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያጋጥመው "የጣሊያን መገናኛ ብዙሀን ቃለምልልሴን አዛብተው አቅርበዋል" የሚል ማስተባበያ መስጠቱን አውስቱአል።

በጊዜው የካቶሊክ የሀይማኖት አባቶች የቃል ኪዳኑን ታቦት አይተው ለማረጋገጥ የሚፈቀድላቸው ከሆነ ለአቡነ ጳውሎስ 25 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል እንደተገባላቸው ተዘግቧል ያለው ኢሳት ገንዘቡ የሚለግሰው "ዳኮስታ ፋውንዴይሽን" በተባለው የኢጣሊያ የኢንዶውመንት ድርጅት በኩል ሲሆን ፣ አቡነ ጳውሎስ ገንዘቡ " በቫቲካን የሚገኘውን አይነት ሙዚየም በአክሱም ከተማ ለማሰራት ይውላል ብሎ" ተናግሮ ነበር ብሉአል።

ኢሳት ቀጥሎም በአቡነ ጳውሎስና በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ባለስልጣናት መካከል እንደ ድልድይ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት በኢትዮጵያ ያደጉት ጣሊያናዊው ጁሊዮ ቢሰሪ ወይም አክሊለ ብርሀን መኮንን የሚባሉት ባለሀብት ናቸው ያለ ሲሆን አቡነ ጳውሎስ ከፖፕ ቤኔዲክት 16ኛ ጋር ሲገናኝ ከአጀቡዋቸው መካከል እኝህ ባለሀብት አንዱ ናቸው። እንዲሁም ጁሊዮ ቢስሪን ወይም አክሊለ ብርሀን መኮንንን ከዘረኛው መለስ ዜናዊና አዜብ መስፍን ጋር የሚያገናኙት ደግሞ ፣ የስዩም መስፍን የጋብቻ ዘመድ የሆነው ቆንስጠንጢኖስ በርሄ ነው ብሉአል።

ቆንስጠንጢኖስ በርሄ ፣ጁሊዮ ቢሴሪ ወይም አክሊብርሀን መኮንን፣ ጊዮን ሆቴልን በ512ሚሊዮን ዶላር ለመግዛት ተስማምቶ የመጀመሪያውን 210 ሚሊዮን ዶላር መክፈል ተስኖት ግዢውን እስካቆመበት ጊዜ ድረስ የባለሀብቱ የኢትዮጵያ ወኪል ሆነው በኦፊሴል አገልግሉአል።

ቆንስጠንጢኖስ በርሄ መለስ ዜናዊን ከውጭ አበዳሪ ድርጅቶች፣ ከቻይና ፣ ከህንድ እና ከሌሎችም አገሮች ጋር የሚያገናኝ ሰው መሆኑ የሚነገርለት ሲሆን አቡነ ጳውሎስ ላለፉት ሁለት አመታት ጉዳዩ ትኩረት እንዳይሰጠው አድርገውት የቆዩ መሆኑንና ፣ ሰሞኑን ደግሞ ለቫቲካን ባለስልጣናት የገቡትን ቃል ተግባራዊ ለማድረግ "የቤተክርስቲያኑ ጣሪያ" ያፈሳል የሚል ሰበብ እንዲነገር ማስደረጋቸውን የውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ።

የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚገኝበት ቤተክርስቲያን ጣሪያው ቢያፈስ እንኳን ጉዳዮ በድብቅ ተይዞ ህንጻው እድሳት ይደረግለታል እንጅ፣ በምንም ተአምር ዜናው ለአለም ህዝብ ሊገለጥ አይገባውም ሲሉ አዋቂዎች ይናገራሉ።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org